# እንደወጡ ያልተመለሱ እንዳዲያቆኑ ያላቀሰሱ

*ቤዝ አሲምባ ፀለምት - ዶሎኪያ ተርናሻ*
*መሰረት ያኖርነው - መነሻ መድረሻ*
*አንዷን ላውሬ ፕሎ - ሌላዋን ለውሻ*
*ሽንፈት አደረገው - ምሽጉን መሸሻ*

ግለሰቦች የየራሳቸውን ገጠመኞች (memoir) ይፅፋሉ። እንደ ስብስብ (as a group) የራሱን ገጠመኝ ( memoir) መፃፍ የማይችል ሕዝብ ብቻ ነው። ገጠመኙን መፃፍ ስላልቻለም ሕዝብ የራሴ የሚለው ታሪክ ኖሮት አያውቅም። በተለምዶ ታሪክ ብለን የምንጠራውም ትርክቱ የሕዝብ ታሪክ አይደለም። ለምን? ቢሉ ታሪክ ፀሃፊዎች ታሪኩን ሲፅፉ ትርክቱን ወይ በገናና ሰዎች የሾረ እንዝርት፤ አለያም በተወሰነ ድርጊት ዙርያ በግለሰቦች የተዘነገገ ዝንግግ ያደርጉታል። ፀሃፊዎቹ ዝንግጉን አጠንጥነው ልቃቂቱን ታሪክ ሲሉን እኛም ታሪክ አድርገን እንወስደዋለን።

ታሪኩ የሚከናወነው በሕዝብ ውስጥ ቢሆንም ትርክቱ ግን የሕዝብ  ቢመስል እንጂ የግለሰቦች መድብላዊ ድርጊት ነው። ሕዝብ ዘወትር የታሪክ  መድረክ ሆኖ ሳለ ትርክቱ  ግን መድረኩን ሳይጨምር የተውኔቱና የተዋንያኑ ትግብርት እየሆነ ይተረካል። በታሪክ ዙሪያ ስለ ህዝብና ገጠመኙ ስናነሳ ወደ ህሊናችን ቀድሞ የሚመጣው የቬትናም ህዝብ ገጠመኝ ይሆናል። ለምን? ቢባል በመስዋዕትነቱም ሆነ በድል ግዝፈቱ በዓለም ወደር የማይገኝለት ትግል የተካሄደው በቬትናም ህዝብ ነበርና።

ለእናት ሀገር ጥርስ ይሰብሩላታል ይሉ ነበር ቬትናማዊያን። በትግላቸው ዘመን። ለየህዝቦቻቸው እንደ ቬትናም ታጋዮች ጥርስ የሰበሩ፤ አጥንት የከሰከሱ፤ ደም ያፈሰሱ፤ ስጋ የቆረሱ፤ ብሎም ህይወት የገብሩ የህዝብ ቤዛዎች ብዙ ናቸው። ግን የብዞዎቹ ትግል እንደ እኛው ግባቸውን ያልመቱ አብዮቶች ማህበርተኛ ከመሆን አላለፈም።

ትንግርተኞቹ ቬታናማዊያን ቀደም የፈረንሳይን የቅኝ ቀንበር በኋላም የአሜሪካንን ኢምፔሪያል ክንድ ሲሰብሩ ዓለምን አስደምመው ነበር። ለዚህ ድል የበቁትም ራሳቸውን የጦር ማገዶ አድርገው እየተቀሰቀሱ ጦርነቱን ከሰሜን ቬትናም ወደ ደቡብ እንዲሸጋገር በማድረግ ነበር። ሰሚናዊያኑ አብዮተኞች ደቡባዊ ወንድሞቻቸውን ወደ ትግሉ ለማስገባት ሲሉ ነበር ጥርሶቻቸውን እንዲሰበሩ የተገደዱት። ደቡብ ቬትናም ውስጥ  አሥር ዓመት ሲሞላቸው የታች ሁለት ጥርሶቻቸውን የማውለቅ ባህል ያላቸው/የነበራቸ ጎሳዎች ነበሩ። ሰሚናዊያኑ በነዚህ ደቡባዊ ወገኖቻቸው መሃል ገብተው አብዮታዊ የህቡዕ ሥራዎችን ለመስራት ህብረተሰቡን መምሰል ስለነበረባቸው ነበር ሁለት ጥርሶቻቸውን እያወለቁ  የተቀላቀሏቸው።

በእኛውም ጭንግፍ አብዮት እንደ ቬትናሞች የአብዮት ማገዶ እየሆኑ ተቆስቁሰው ያለቁ አያሌ ነበሩ። ብዙ ወጣት ኢህአፓዎች የህዝባቸውን ነጻነት እየተመኙ እንደ ቬትናማዊያኑ ህዝቡን መስለው የህቡዕ ሥራዎችን ለመስራት ወደ ህዝቡ ጎርፈዋል። ሴቶቹ ረዥሙን ፀጉራቸውን ቆርጠው እንደ ጎጃሞች ጋርሰ፤ ወይም እንደ ጎንደሮች ጋሜና ሹርባ አለያም እንደ ትግሬዎች ቁንን እየተሰሩ፤ እንደ ህዝቡም በባዶ እግራቸው ተጉዘው፤ ጥሬ ቆርጥመው፤ ከጭቃ መደብ ላይ ተኝተው፤ ቅማል ቀምለው፤ እከኩን አክከው፤ ቅጭጭቱን ተቀጭጨው ወንዶቹም ሆኑ እሴቶቹ የህዝቡን ኑሮ እየኖሩ ነበር በትግሉ የተሰማሩት። ከነዚህ ውስጥ ማሬ አረጋ አንዷ ነበረች።

ማሬ የባህር ዳር ልጅ ነች። አባቷ አቶ አረጋ ወርቅነህ ባህርዳር ከተማ ውስጥ በወቅቱ አሉ ከሚባሉት ትልልቅ ሆቴሎች ያንደኛው ባለቤት ነበሩ። ማሬም ቅምጥል የሃብታም ልጅ ነበረች። ቦርቃቃ ኮረዳ። ዜንጦ የፒያሳ ልጅ። ግን አብዮቱ መጣና ጥሩዋን አደፈረሰው። የዘመኗ ወጣት በህዝብ ፍቅር ነዶ ባደባባይ እየተመመ

በዱር በገደሉ ፋኖ ተሰማራ
እንደ ሆቺሚኒህ እንደ ቼ ጉቬራ

ብሎ ሲዘምር እርሷንም ፋኖ ትሆን ዘንድ መዝሙሩ ልቧን አሸፈተውና አይገዛም ህዝቡ እስከ መጨረሻ፤ ለእስራኤል ቡችላ ላሜሪካ ውሻ ብላ ዘመረች።  ልቧም ድል ሰንቆ ወደ በርሃው ነጎደ። አሲምባ ተራራን አሸጋግሮ የሚያየው ህሊናዋ ህይዎቷን የህዝብ ቤዛ ታደርገው ዘንድ ቃል አስገባት። በብስክሌት ተወዳዳሪነት የገነባችውን የግል ዝናም እንድትንቀው አደረጋት። እናም ሌት ሌት በጨለማ፤ ቀን ቀንም በከለላ በህዝብ መሃል ገብታ በማደራጀት ሥራ ባዘነች። ውሎ አደሮ ሥራዋ እንቅስቃሴዋን አጎላውና ማንነቷን አሳወቀው። እናም ከብስክሌት አልፋ  እግሬም ኮረኮንቹን መንገድ ልመደው፤ ጎኔም ከመደቡ ምኝታ ጋር ተዋወቅ፤ ሆዴም ከእንግርግቡ ( አሹቅ ) ጋር ተዋዛ፤ እጆቼም ለመፍጨት መጁን ተዋወቁት. . . . ለማለት እድሉን ሳታገኝ ተጋለጠችና ወደ ሜዳ እንድትወጣ ተወሰነ። አንድ ምሽት ላይ ልትያዝ መሆኗ

ተነግሯት ህቡዕ ገባች። በዚሁ የህቡዕ መጠለያ ጥቂት ቀናት እንደቆየች ወደ አሲምባ እንደምትወጣ ተነገራትና ጎዞዋን በጉጉት ትጠባበቅ ጀመር። ከዕለታት ባንደኛዋ ምሽት የባላገር ቀሚስና ነጠላ ከባራባሶ ጫማ ጋር የአለባበስ ልምምድ ታደርግ ዘንድ ተሰጣት። ልብሶቹ እንደ ደረሷትም ቀሚሱን አጥልቃ በመቀነቱ ሸበክ አደረገችና ባራባሶውን ተጫምታ ነጠላውን ና ተለበስ ብትለው አላውቅሽም አላትና በተለበስ አልለበስም መሃል ግብ ግቡ ቀጥሎ አመሸ።

ያን ዕለት ሌሊቱን እንቅልፍ በዓይኗ ሳይዞር አደረ። ሌሊቱን ሙሉ ቀዩን ሠራዊት አሲምባ ላይ ተቀላቅላ አቀበቱን ስተወጣና ቁልቁለቱን ስትንደረደር አደረች። እረፋዱ ላይ የሆነ ደረቅ ዳቦ በመዝጊያው ስር ተወረወረላት። በጋዜጣ ተጠቅልሎ ያገኘችውን ዳቦ ና ተነከስ ስትለው ግን አልደፈርሽ አላት። ግን ከደረቁ ዳቦ ጋር መለማመድ ነበረባትና ባፏ እየዞረም ቢሆን ጨረሰችው። በሂደት ግን ጉረሮዋና ዳቦው እየተዛመዱ መጡ። ማታ ማታ ጓዱ ሲመጣ ስለ ውጨኛው ዓለም ስትጠይቀው እርሱም ማወቅ የሚገባትን ሲነግራት ሰነበቱና

ፍትፍቱም ይቀራል በቀሪው ሊበላ
ቅንጨውም ይቀራል የኋላ የኋላ
ድሎትና ቅንጦት ደህና ሰንብች ብሎ
በቂጣ ይተካል አለያም በቆሎ

እንዲሉ ከችግሩ ጋር መተዋውቋ ቀጥሎ ሰነበተና የጉዞው ቀን ደረሰ።

አንድ ቀን አመሻሹ ላይ ሌሎች ጓዶች ተጨመሩና ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ገሰገሱ። ከተማውን ለቅቀው ጥቂት እንደ ተጓዙ አንድ ቦታ ላይ ይጠብቃቸው የነበረው መስመረኛ ተቀበላቸውና የሌሊቱን ጉዞ በአዲስ ሞራልና ጉልበት ተያያዙት። ሌሊቱ ተዋግዶ ከዶሮ ጩኸት በፊት አንድ መንደር ውስጥ ገቡ። መንደሩ ውስጥ እንደገቡ መስመረኛው በሞተ ድምፅና ኮቴ እንዲራመዱ በሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ተራምደው አንዲት ጎጆ ውስጥ ገቡ። እንደገቡም በያሉበት ተዘረሩ።

እረፋዱ ላይ የጎጆዋ መዝጊያ ሲከፈት ባሰማው ድምጽ ነበር ተቀሰቀሰው የነቁት። እንደ ነቁም የብረት ምጣድ የገብስ ቂጣ ተልባ ተቀብቶ ቀረበላቸው። ምግቡን ሲያዩ ሁሉም ፊታቸውን አኮሳተሩ። እጆቻቸውም ምግቡን ሲያዩ አነከሱ። ሁኔታቸውን የተመለከተው መስመረኛ ግን ይህ የተሻለው ማዕዳችን ነው፤ የከፋው ገና ወደ ፊት ይጠብቃችኋል አለና የድርሻውን ከቂጣው ቆርሶ መመገብ ጀመረ። አነጋገሩ ባንድ ወቅት እርሱም እንደ ነርሱ ከተሜ እንደ ነበር አስገንዝቧቸው እነርሱም እርሱን እንደሚሆኑ ታስባቸውና እጆቻቸውን ሰነዘሩ። አይበላ የለም ያ ቂጣ በውሃ እየታጠበ ወረደ።

ለምሳ የቀረበላቸው ደግሞ የባቄላ እንግርግብ ( አሹቅ) ነበር። አንዳንዶች በይሉኝታ ቁንጥር አድርገው አንድና ሁለት ጥሬ ወደ አፋቸው መወርወር ጀመሩ። ከፊሎቹ ግን አያሳየን ለማለት ይመስላል ሸፍንፍን ብለው መልሰው ጎናቸውን ከወለሉ ጋር አገናኙ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ መስመረኛው ጓድ መጣና ማነቃቂያ የሚሆን ጥቂት ገጠመኞችን አካፈላቸው። በዚህ የገጠመኝ ጭውውት የተጀመረው መነጋገርም ወደ ዜና መቀያየር ተለወጠና እነርሱም ስለ ገጠሩ ትግል፤ ስለ ቀዩ ሰራዊት፤ እርሱም ስለ ከተማው ትግል ማወቅ የሚፈልጉትን እየተጠያየቁ ጊዜውን ገፉት። ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ከጧት ቁርስ የተረፈው ቂጣና እንግርግብ ባቄላ ለእራት ቀረበ። ከራት በኋላም ጉዞ ተጀመረ። ካዲስ አበባ ወደ አስመራ የሚወስደውን አውራጎዳና ወደ ቀኝ እየተው ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ የይልማና ዴንሳን ወረዳ ሰንጥቀው አጼት ከተማ ወደ ደቡብ ስትቀር ከባህር ዳር በወጡ በሶስተኛው ቀን ደብረታቦር አካባቢ ደረሱ።

ጧት ሲነቁ ካዲሱ ጣቢያ መስመረኛ ጋር ተገናኙ። ስላለፉት ጉዞዎች ከጠየቃቸው በኋላ ስለቀጣዩ ጉዞ የተፈጠረውን ችግር አካፈላቸው። እንዲህ ሲል፤ ወደ ፊት ሄደው ሊያርፉበት ይችሉ የነበረው ጣቢያ እንደተጋለጠና ሌላ መስመር እስኪ ዘረጋ እዚህ መጠለያ ሁላቸውንም ማቆየት አደጋ እንደሚኖረው ግልጽ አደረገላቸው። ለደህንነታቸው ሲልም ነጣጥሎ በጊዚያዊ መጠለያ በየግል አርሶ አደሮች ቤት ሊያቆያቸው ሁኔታው እንዳስገደደው አስገነዘባቸው። እነርሱ ግን በሰሙት ወሬ ደስተኛ አልነበሩም። ግን ምርጫ ስላልነበራቸው ሁሉም ወደ የምድባቸው ጉዞ ጀመሩ። ማሬ አረጋም ወደ አንድ ሃብታም ገበሬ ቤት ተወስደች። በቤት ሰራተኛ፤ በገረድ መልክ።

ከቤተሰቡ መሃል ጓዲት መሆኗን የሚያውቁ የቤት ዕመቤቷ ብቻ ነበሩ። ማሬም ይህኑ ምስጢር ተነግሯት የግርድና ኑሮዋን "ሀ" ብላ ጀመረች። በጧት ተነስቶ የጥጆቹን ሽንትና እበት መጥረግ፤ አመዱን ማፈስና ወለሉንም ማጽዳት፤ ለዕረኞቹም ሽሮ አፍልቶ፤ ለገበሬዎቹ ምሳ መቋጠር የዕለት ተዕለት ተግባሮቿ ሆኑ። ማታ ማታም አባውራው ወደ ምኝታ ከመሄዳቸው በፊት ውሃ ወዝቶ እግራቸውን ማጠብና እግራቸውንም መሳም የምሽቱ ሙያዋ ሆነ። ማሬና እመቤቲቱ የሚነጋገሩት ወይ ጧት ሰራተኞችን ከሸኙ በኋላ አለያም ማታ ሁሉም ወንዶች መተኛታቸውን አረጋግጠው ነበር። ያም ሆኖ ከስጋት ጋር እየታገሉ።

በሂደት ሴት ሠራተኞችን ቀረበቻቸውና ፊደል አስቆጠረቻቸው። በፆታቸው ስለሚደርስባቸው ጭቆናም ታስተምራቸው ጀመረች። ዕመቤቲቱም ተሳታፊ ስለሆኑ የካድሬነት ሥራዋ እየጎላ ሄደ። የግርድና ተግባሯም በሌሎቹ ገረዶች እገዛ እየቀለለ መጣ። ። የጎረምሳዎቹ ጉዳይ ግን ቤቱን እስከ ለቀቀችበት ጊዜ ድረስ ቀን በቀን የምትፋለመው ጦርነት ሆኖ ቀጠለ።

## የግንኙነት መቋረጥ

የሁለተኛው ጣቢያ መስመረኛ ጓዶችን ለመቀበል አዴት አካባቢ ወደሚገኘው መጠለያ ጎራ ሲል ጣቢያው ተበልቶ ኖሮ ድንገት በጠላት እጅ ወደቀ። ይህም ችግር በራሱ ሌላ ችግር ፈጠረ። የጠፋውን ጓድ ተረገጥ ለማግኘት የሦስተኛው ጣቢያ መስመረኛም ከመዋቅር ውጭ ግንኙነት ለመቀጠል ሲጣድፍ በገበሬ ማህበር እጅ ወደቀ። እነዚህም ተደራራቢ ችግሮች ለማሬ የሰቆቃ ህይዎት እድሜ ሲጋሽ ሆኑ።

በዚህ ሁሉ መሃል እመቤቲቱ የማሬን ችግር ለማቃለል የቦዘኑበት ጊዜ አልነበረም። አንዳንዴ ችግሩን ያቃለልኩ መስሏቸው ትንሿን ቡይት አሸክመው ውሃ እንድትቀዳ ወደ ወንዝ ይልኳት ነበር። ምናልባትም በዚሁ አጋጣሚ ጓዶቿን ታገኝ ይሆናል የሚል ተስፋ ሰንቀው ይሆናል ማሬን ወደ ወንዝ ይልኳት የነበረው። እርሷም ተስፋዋ ዕውን ይሆን ዘንድ ጊዜ ፈጅታ ነበር ወደ ቤት የምትመለሰው። ግን ተስፋቸው ከቀን ወደ ቀን እየመነመነ መጣ። እመቤቲቱ ግን ግርድናው እንዳይሰማት ብዙ ጣሩ። ግርድናዋን ግን ከትከሻዋ ሊያወርዱላት ባለመቻላቸው ሁሌም ይጨነቁ ነበር። ከሴት ሠራተኞቹ ጋር የተፈጠረው መልካም ግንኙነት ድሮ ትፈጨው የነበርውን እህል እንዳትፈጭ አድርጓታል። በምትኩ ትንሽ አተር ወይም ባቄላ ይሰጧትና መጅን በማንቀሳቀስ እየፈጨች ያስመስሏት ነበር። በዚህ መሃል ከዚህ መጣ የማይሉት ቁስል የማሬን ገላ አነፈረው። ይህም ድንገተኛ በሽታ ቀዩን ሠራዊት የመቀላቀል ምኞቷን ስላጨለመው ህሊናዋ ተረበሸ። እመቤቲቱም ሁኔታዋን አይተው ይበልጥ ተጨነቁ።

የሴት መላ የጉንዳን ጉልበት ይስጥህ እንዲሉ ይመስላል ከዕለታት ባንደኛዋ ቀን እመቤቲቱ ተነስተው ወደ አንድ ዘመዳቸው ቤት ይሄዱና ስለ ኢህአፓዎች ባካባቢው መኖር ዳር ዳር እያሉ ወሬ ጀመሩለት። ዘመዳቸውም የማሬን ነገር ያውቅ ኖሮ የመስመር ችግር እንደ ነበርና ችግሩም መቃለሉን ይነግራቸዋል። ከዚያም ጉዳዩን በግልጽ ተወያይተውበት ማሬ አረጋ ማታውኑ ወደ ሰውየው ቤት ሄዳ እንድታድር ይወስናሉ። ወደ ቤታቸው ተመልሰውም እቅዱን ለማሬ አጫወቷት። ሁሉም ነገር ተከናውኖ ቤተሰቡ ሲተኛ ጠብቀው ይዘዋት ወጡ። ከዘመዳቸው ጋርም አስተዋወቋት። ከዚያም ሁለቱ አርሶ አደሮች ከማሬ ገለል ብለው ስለ ጉዞዋ መነጋገር ጀመሩ።

ጎዞውን ሲያስቡት ገና ከጅምሩ የሰቀቀን ጎዞ ሆነባቸው። በእግሯ አይልኳት ነገር በባዶ እግር ቤት ለቤት እንጂ እርቀት ያለው መንገድ መሄድ አልተለማመደችም። በጫማ እንዳትጓዝ ቁስሏ ጫማውን አታስነኩኝ ባይ ነው። በፈረስ ላማጓጓዝም በቀን መጓዝ ሊኖርባት ሆነ። መንገዱ አውራ መንገድ ነውና የሚመጣውም ሆነ የሚሄደው መንገደኛ ስለሚተዋወቅ በመንገድ ላይ የሚያውቁት ሰው ቢገጥማቸው ይህች ልጅ ምንህ ነች? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ፈረስ ይዞ በጨለማም አቀበት መውጣትና ቁልቁለት መውረድ ይከብዳል። መከበድ ብቻም አይደል አደጋም አለው። ፈረሱ ድንገት ኮሽታ ሲሰማ ሊደነብር ይችላል። ዞሮ ዞሮ መከራው ከማሬ ትከሻ ላይ አልወረደም አሉና በባዶ እግርና በጫማ በፈረቃ ሞክሪ ሊሏት ወሰኑ። እናም ነገሯት።

ለእናት ሀገር ጥርስ ይሰበርላታል እንዳሉት ቬትናማውያን ማሬም እግሮቿን ልትመላልጥ ወስና ይልቁን ጉዞው መቼ ነው? ስትል ጠየቀቻቸው። ሁሉም ነገር እንደተሳካ አሏት እመቤቲቱ ቀልጠፍ ብለው። ከዐይኖቻቸው ውኃ እየተቀዳ አትኩረው ሲያዩዋት አሳዘነቻቸውና በወገባቸው ተጠመጠመች እጃቸውን እያሻሸች ጓዲት ከቤቴ ስወጣ ለዚህ ሁሉ ተዘጋጅቼ ስለወጣሁ አትጨነቂ። ይልቁን ጫማ እግሬን የምጠመጥምበት ጨርቅ አፈላልጊ አለችና ዕምባቸውን አብሳ ሳመቻቸው።

እርሳቸው ግን አተኩረው እየተመለከቱ የምትላቸው ሁሉ ሆድ አልሆን ስላላቸው ሰቅ ሰቅ ብለው አለቀሱ። እቅፍ አድርገውም አወይ ወላድ መሆን፤ አወይ የናት አንጀት፤ እኔም እንደ እናትሽ ሬሳሽ ከቤቴ ሲወጣ ላለማየት ስል ጓዶችሽን የበላ ጅብ ይብላሽ ብየ ከቤቴ አስወጣሁሽ ብለው በዕምባ ይታጠቡ ጀመር። ምነው አፈር በበላሁ። ምነው ባላወቅሁሽ። በቁምሽ ቀበርኩሽ አሉና ማሬን ከደረታቸው ለትመው ተንሰቀሰቁ። ለማሬም ይህ ስንብት የጓዷም የናቷም ሆነባትና ዐይኖቿ ውኃ ሞሉ። በመጨረሻም ጉንጭ ለጉንጭ ተሳስመው ተለያዩ። እመቤቲቱም ዕምባ በሚያጎርፉ ዐይኖች እየተከተሉ ሸኟት። ማሬና መሪዋ ደብረታቦርን ወደ ደቡብ፤ እብናትንም ወደ ምዕርብ እየተው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ በለሳ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሀሙሲትም ደረሱ። ሀሙሲት በሊቦ አውራጃ በዝዊ ወረዳ የምትገኝ የገጠር ከተማ ነች። ከሀሙሲት ወደ ሰሜን ምስራቅ ተከዜን ሲሻገሩ ወሎ ይሆናል። ሰቆጣ።

## ሀሙሲትና ህክምና

አይደረስ የለም ሀሙሲት ተደረሰ። ወደ ህክምና ጣቢይውም ተወሰደችና ህክምናው ተጀመረ። በጣቢያው ያየቻቸው ጓዶች ግን ሀዘንና ብስጭት የተቀላቀለበት ስሜት አሳደሩባት። ስለ ሁኔታቸው አዘነች። ሁሉም ነገር ከጠበቀችው በታች በመሆኑም ግራ ተጋባች። የጠበቀችውን ቀይ ሠራዊት ስላልነበረ ያየችው ተስፋዋን አጨለመው። የወደፊቱም ጉዞዋ በምታየው ስእል አምሳያ ተሳለባት። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች አንድ ምሽት እራት ቀርቦ በገበታው ዙሪያ ተቀመጡ። ሁሉም እጁን ወደ ገበታው ሲሰድ እርሷም እጇን ስትልከው ያንደኛው ጓድ ፊት ሲለዋወጥ ዐይን ለዐይን ተጋጩ። እጇን ሰብሰብ አድርጋ ተነሳችና ወደ ጎጆዋ ሄዳ መጽፍ ጀመረች። አንድ ሁለቱ ተከትለዋት ሄዱና

ሊይጽናኗት ሞከሩ። እርሷ ግን ጓዶች ሰው መሆኑን አትርሱ። አስቦት ሳይሆን ሳያስበው ነው ሰውነቱ የተፀየፈኝ አለቻቸው። ማታውኑ ወሬው ጣቢያውን አዳረሰውና ሁሉም ዓለሚቱን ከበቧት። የነፈረውን ሰውነቷንም አይተው አዘኑላት። ከዚያች ምሽት በኃላ ከዓለሚቱ ጋር ለመመገብ ጓዶች ይሽቀዳደሙ ጀመር።

ዓለሚቱም (ማሬ አረጋ) በሃሙሲት ቆይታዋ ብዙ ነገር አስተዋለች። ካስተዋለችው አንዱ ነገር በጣቢያው ከሚገኙት በሽተኞች  የሚበዙት ሴቶች መሆናቸውን ነበር። እናም ለምን ይሆን? ስትል  አስተውሎቷን በማስታወሻዋ አሰፈረችው። ከፊሉን በግጥም ከፊሉን ደግሞ በስድ ንባብ። አንድ ቀን ከራት በኃላ ለምን ይሆን ሴት ጓዲቶች በጣቢያው የምንበዛው? ስትል ጥያቄውን አነሳችላቸው። ከመሃከላቸው አንደኛው ጓድ ብዙዎቹ  ከጾታ ጋር በተያያዘ  ነው። ከኔ ይልቅ ግን ጓዲቶች ብታስረዷት ይመረጣል አለና ጥያቄውን መልሶ ወደ ሴቶቹ ወረወረው። አዎ አለች አንደኛዋ ጓዲት። አዎ በርግጥም እንደተባለው የጾታ ባህሪይ አለው በሽታችን። ጋኣት እንለዋለ። ጋኣት ከወር አበባ ጊዚያዊ መቋረጥ ጋር የተያያዘ በሽታ ነው። ብዙውን ጊዜ ጓዲቶች የወር አበባ ሳናይ ለሁለት ወርና ለሶስት ወር ከዚያም በላይ እንቆያለን። ጋኣት ያመማቸው ጓዲቶች የበሉት ከሆዳቸው አይቆይም። ወዲያውኑ በገባበት ቡልቅ ብሎ ይወጣል። ሆዳቸው እርጉዝ እስኪመስል ይወጠራል። ውስጣቸውንም ጥሩ ስሜት አይሰማቸውም። ያስጨንቃቸዋል። በተለይ በሠራዊቱ ወስጥ የሚንቀሳቀሱ ጓዲቶች ከትጥቅ ጋር ብዙ መበገሰ (መጓዝ) ይከብዳቸዋል፤ አለችና ጥያቄሽን መለስኩልሽ? ስትል ዓለሚቱን ጠየቀቻት።

አዎ የኛ ትግል ገና ብዙ ዓመታትን የሚጠይቅ ሆኖ ነው የሚታየኝ። አፈጣጠራችን በራሱ ሙሉ ሰው አያደርገንም። ከአዳም ግራ ጎን ተፈልቀን እንደ ተፈጠርን ነው ቅዱስ መፅሃፍ የሚገልፀው ስትል የዕምነት ቀለም ቀባችው። ዓለሚቱ። ሌላዋ ጓዲትም ቀጠል አድርጋ ሴትነታችን በህብረተሰቡ ዐይን ግማሽ ሰው ሆነን እንድንታይ ሃይማኖቱ እየሰበከ እኩልነታችን አልተከበረም ስንል የምንታገለው አገዛዙን ብቻ አይመስለኝም። ሃይማኖቱንም ጭምር እንጂ። ጭቆናችን ድርብ ድርብርብ ነው ስንል ዕምነቱ በስብከት፤ ሥርዓቱ በትምክህት፤ ተፈጥሮም በዕናትነት (በወላድነት) ስለሚረገጡን ይምስለኛል። እኛ እንኳ ታግለን  ነጻ ብንወጣ ሁሉም ሴቶች ነጻ ወጡ ለማለት አያስደፍርም። ሁሉም ሴቶች ነጻ እንዲወጡ በዓለም ዙሪያ የተቀነባበረ ትግል መካሄድና ከዕምነት እስከ ሥርዓት መለወጥ ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ዕውን ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም። አብዮት ዓለምን ባንዴ ማጥለቅለቅ አይቻለውምና።

ጭብጥና ቡርጋንዴ

በዚህ መልክ ዘወትር ከእራት በኋላ የተለያዩ ርዕሶች እየተነሱ ውይይት ሲካሄድባቸው ሰነበቱና በመጨረሻም ህክምናዋን ጨርሳ ወደ ተአሊም (ውታደራዊ ስልጠና) ተላከች። በስልጠና ላይ እያለች ቀደም ሲል ጀምሯት የነበረው የአእምሮ ህውከት እየከፋ መጣ። ስልጠናውን እንደጨረሰችም እርሷ ደሳለኝና ኮከቤ ከሌሎች አሥራ አንድ ጓዶች ጋር  በወልቃይት ቀጠና ተመደቡ። ወደ ወልቃይት ሲጓዙ ተርናሻ ላይ ሠራዊቱ ተሰብስቦ ሲወያይ ደረሱ። የሠራዊቱን ተርናሻ ላይ መሰብሰብ ሲጠይቁ በማይፀምሪው ድርጊያ ( operation) የተሰውትን ሰማዕታት ለመዘከር እንደሆነ ተነገራቸው። ዓለሚቱ ይህን እንደ ሰማች ቅልቅል ስሜት ተሰማት። ባንድ በኩል ለሰማዕታታቱ የሚሰጠው ክብር አስቀናት። በሌላ በኩል ግን የጦሩ ሁኔታ አሳዘናት።

የከተማ ጓዶች አስፋልት ላይ ተጥለው የውሻ መራኮቻ ይሆናሉ በሠራዊቱ ግን ህይዎትና ሞት ተሳስመው ሲለያዩ ሥርዓቱ እንዲህ ይከበራል ስትል ለራሷ ነገረችው። ከተማ ሳለች ስለ ቀዩ ጦር ትሰማው የነበረውም ተስብስቦ ከምታየው ጎስቋላ ወታደር ጋር አልዛመድ አላትና አስቆዘማት። እናም ነገሩን ሁሉ ስታየው ዊሊያም ሸክስፒር እንዳለው ምንም ለማይፈይድ ነገር ብዙ መከናወት ( much ado about nothing) ሆነባትና ዘወትር ስሜቷ ሲነካ እንደ ምታደርገው ብዕሯን እንዲህ ስትል አስለቀሰችው፡

የሰማሁት ሌላ የማየው አስለቃሽ
ራሴው አድርጎት እኔውን ተወቃሽ
የእከኬን ጠባሳ የትናንቱን ቁስሌን
ይቅርታ ጠየቅሁት ማረኝ ብዬ አካሌን።

የዕኩለ-ቀን ላይ ጨለማ ( darkness at noon)

የፀለምቱ ቆይታዋ በዚህ ተገባድደና ወደ ወልቅይት አቀናች። ወልቃይት እንደ ገቡም ምድቧ ሀይል አምስት ውስጥ ሆነ። በሃይል አምስት ውስጥ ለዓመት ያክል እንደቆየች ለህክምና ወደ ደለሳ ቆቃ ጣቢያ ተላከች። በህክምና ጣቢያው ከነበሩት ከወደሬ፤ ከአበራ፤ ከፍሬወይን፤ ከደሳለኝ፤ ከከበደ፤ ከደምስና ከመሸሻ ጋር ህክምናዋን እየተከታተለች ለተወሰነ ጊዜ ቆየች።

ከነዚህ ህመምተኖች መሃከል መሸሻና አበራ መንቀሳቀስ አይችሉም ነበር። መሸሻ አንድ እግሩን በጦርነት አጥቷል። አበራም አንድ እግሩ ክፉኛ ቆስሎ ይጸዳዳ የነበረው ከተኛበት መሬት ስር ጉድጓድ ተቆፍሮ ከጉድጓዱ ውስጥ የሽንትና የዐይነ ምድር መቀበያ ዕቃ እየተቀመጠለት

ነበር። ዓለሚቱም ወደዚህ ህክምና ጣቢያ ከመጣችበት ጊዜ ጀምሮ ጣቢያውን እስከ ለቀቀችበት ጊዜ ድረስ የአበራ የግል “ነርስ” ነበረች ማለት ይቻላል።

አበራ ቁስሉ ይንዠከው ስለነበር እንቅልፍ አይተኛም። ዓለሚቱና ከበደ ነበሩ እንቅልፍ የሚያስይዙት። ከበደ ድሮ ያያቸውን ሲኒማዎች ይተርክለታል። ዓለሚቱ ደግሞ በግጥም ህመሙ ተሽሎት ነገ መራመድ እንደሚችልና ብሎም ለውጊያ እንደሚሰለፍ ተስፋ ትሰጠው ነበር። አልፎ አልፎም ስለከተማው ትንቅንቅ ትርክቷን ስታካፍለው ለተወሰነች ሰዓትም ብትሆን ያሽልባል። ገጠመኟንም ከ “ሀ” እስከ “ፐ” ያጫወተቻቸው በዚህ ወቅት ነበር።

ዓለሚቱ ከእዕምሮ በሽታዋ በተጨማሪ ሌላም ህመም ነበረባት። ሌሊት ሌሊት ሳትነቃ ከምኝታዋ ተነስታ የመሄድ (sleep walk) በሽታ። ደለሳ ቆቃ ህክምና ጣቢያ በነበረችበት ወቅት አንድ ሌሊት ተነስታ ወደ አንድ መንደር ዘልቃ ገባችና አንድ ቤት ውስጥ ቡና እየተቆላ ደረሰች። ባለቤቶቹም እንዳዩአት ደንግጠው ከተቀመጡበት ተነስተው ውሾቹ እንዴት አሳለፉሽ? ሲሉ ጠየቋት። ራሴን ያወቅሁት ከቤት ከገባሁ በኃላ ስለሆነ ከዚያ በፊት ስለሆነው ሁሉ አላውቅም። ያነቃኝም የቡናው ሽታ ነው አለቻቸው።

አርሶ አደሮቹም በሁኔታዋ አዝነው አስቀመጧትና እህል ውኃ ቅመሽ አሏት። ዓለሚቱ ግን ከነቃች በኋላ ራሷን ሳተችና እህል ውኃ መቅመስ ቀርቶ መቆምና መራመድ አቃታት። አርሶ ስደሮቹም በሁኔታዋ ተደናግጠው ወደ ጣቢያው ተሸክመው ወሰዷት። ስለ ህመሟም የሰሙት ካዩት ጋር ተዳብሎ በጅጉ አሳዘናቸው። ሌላ ጊዜ ደግሞ ከጣቢያው ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ወንዝ ወርዳ እግሯን ታጥባ ከወንዙ ዳር ተኝታ ተገኘች። ከነዚህ ሁለት አጋጣሚዎች በመለስ ምን ጊዜም ሌሊት ወጥታ ስትመለስ ዓለሚቱን ያጋጠማት ችግር አልነበረም።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ነበር ወያኔ ወልቃይት ውስጥ መግባቷን የሰሙት። የወያኔ ወልቃይት መግባት የከባቢውን ፀጥታ ስላደፈረሰው ህክምና ጣቢይው እንዲዘጋና በሽተኞቹም አስተማማኝ ፀጥታ ወደ ሚገኝበት ቦታ እንዲሄዱ ተወሰነ። መንቀሳቀስ የሚችሉት ወደ ጸለምት ተላኩ። መንቀሳቀስ የማይችሉት መሸሻና አበራ ዋልድባ ገዳም ውስጥ ህቡዕ ገቡ። መንቀሳቀስ የቻሉት ጸለምት እንደገቡ ዓለሚቱ ከፀለምት ሀይሎች ጋር ላጭር ጊዜ ከተንቀሳቀሰች በኋላ በሬዲዮ ግንኙነት ክፍል ተመደበች። በዚሁ በሬዲዮ ግንኙነት ምድቧ እንዳለች ለህመሞቿ ትወስዳቸው የነበሩት መዳህኒቶች በሰውነቷ ውስጥ የርስ በርስ ግጭት መፍጠር ጀመሩ።

ዓለሚቱም ድሮ ይሰማት ከነበረው ህመም የተለየ ስሜት እየተሰማት መጣ። የሰውነት መዛልና ድካም አዘውትረው ይጎበኟት ጀመር። በዚህም ምክኒያት ወደ ጣራ የህክምና ጣቢያ ተወሰደች። ከዕለታት ባንደኛዋ ቀን ከጓዶች ጋር ምሳ በልታ ጥቂት እንደቆየች በቁሟ ወደቀች። አጠገቧ የነበሩት ጓዶች ደርሰው ሊያነሷት ሞከሩ። ዓለሚቱ ግን የወደቀችው እስከ ወዲያኛው ዳግም ላትነሳ ነበርና ወዲያው አንድ ጓድ ጥይት ተኮሰ። ባካባቢው የነበሩት ጓዶች ተሰባሰቡና ለዘመናት እየተዘመረ በወታደራዊ ሥነሥርዓት ሬሳዋ ወደ መቃብር ወረደ።

ማሬ አረጋ ይህችን ዓለምና ትግሉን እንዲህ ተሰናበተቻቸውና እርሷም እንደ ወጡ ያልተመለሱ ከሚባልላቸው ኢህአፓዎች አንዷ ሆነች። መሸሻ፤ አበራና የቀሩት ቁስለኞችም ትግሉ ገርገጭ ሲል እንዳዲያቆኑ ያላቀሰሱትን ጓዶቻቸውን ተቀላቅለው ተሰደዱ። ከንቱ ትግል። ከንቱ ደም። ከንቱ ህይዎት። የባከነ ትውልድ እንዲሉ።

የሰማዕታቱን ነፍስ ይማር።

ታህሳስ 2006

abraham3106@comcast.net